ጥር 4 ቀን 2003 ዓ.ም

## የድርጅቶችን ገበና ለወያኔ ማስጣቱ ጎጂ ነው

በታጋይ ድርጅቶች ውስጥ የየሚከሰቱ ድክመቶችንና ችግሮችን በተመለከተ ገንቢ ትችቶችንማቅረቡ ተገቢ ቢሆንም በአደባባይ ብሎም መሆን በሌሌበት ደረጃ ገበናን አስጥቶ መቦጫጨቁ ጠቀሜታው ለሀገርና ለሕዝብ ጠር ለሆነው ለወያኔ በመሆኑ ኢሕአፓ ይህ ድርጊት እንዲቆም ማሳሰቡ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል።

በአሁኑ ጊዜ ለሕዝብና ለትግል አሳቢ መስለው ችግሮችን ለማባባስ በመሰሪ መንገድ መጮህ የጀመሩ መኖራቸውን እያየን ነው። በድርጅት ደረጃ መኢአድ ተከፋፈለ በሚል ይህን ያን ደገፍን በሚልም ሽፋን ሁሉንም አደባባይና ክፍፍሉን አጠናካሪ ተንኮልን የሚረጩ አሉ። ለመኢአድ ችግር በተዓምር ኢሕአፓን ተጠያቂ አድርገው የሚከሱና የሚቧርቁም እንዳሉ መስማት ችለናል። የአርበኞች ግንባርን አስመልክቶም የሚሰማው ጫጫታ ጤነኛ አለመሆኑና በመሠረቱ የወያኔን ልብ የሚያሞቅ መሆኑ የሚታይ ነው። ለዚህም ነው ወያኔ ይህን ክስተት በራዲዮና ቴሌቪዥን እያስተጋባው ያለው። መሰሪው ወያኔ የድርጅቶች ክፍፍል ወይ ችግር ሲከሰት ሰርጎ ገቦቹን እያንቀሳቀሰ ይህንና ያኛውን ደጋፊ እየመሰለ ቅራኔን እንደሚያባብስ አሁንም ያልተረዱ መኖራቸው በጣም ያሳዝናል። አንዳንዶች ደግሞ ምንም እንኳን ለሀገር ተቆርቋሪ ነን ቢሉም ከራሳቸው አልፎ ለማንምና ለምንም ግድ የሌላቸው በመሆናቸው እንደደነበረ በሬ ሁሉን እየወጉና እያጠቁ ጎጂ ሥራን እየሠሩና ወደዱም ጠሉም ወያኔን እየጠቀሙ መሆናቸውንም መጥቀሱ አስፈላጊና ወቅታዊ ነው። የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ በማጤን ጠላትና ወዳጅን በመለየት፥ የዛሬን ዋና ግብ ከነገው ተልዕኮ ባለማደባለቅ፤ ወዳጅን ለመጨመር ለማብዛት በመነሳት መደረግ ያለበትን እንቅስቃሴ መገንዘብ ያቃታቸው ክፍሎች ለገበያው ጭብጨባ ጆሮ ሲሰጡ ለወያኔ በመጎንበሳቸው ድጋፍ ያጡ ክፍሎች ደግሞ ቀዳዳ አገኘን በሚል እንደ ጨጎጊት በሕዝብ ጎራ ላይ ሊጣበቁና ነፍስ ሊዘሩ ሲጥሩም እየታዘብን ነው።

ይህን አሳሳቢ ሁኔታ ስናይ ለሀገር ወዳጁ ሁሉ አደብ እንግዛ፤ ገበናችን ለወያኔ አይሰሸጥ የሚል መልዕክትን ማስተላለፉ አስፈላጊ ሆኖ ታይቶናል። ድርጅቶች በተቻለ መጠን ችግራቸውን በውስጣቸው መፍታት መቻል ያለባቸው ሲሆን ሕዝብን በሚያሳዝን ደረጃ እስከ ቡጢ እየደረሱ ለወያኔ መሳለቂያ መሆናቸውም መቆም ያለበት ነው። ሀላፊነት በጎደለው መንፈስም የድርጅቶችን ውስጣዊ ጉዳይ በአደባባይ እያሰጡና በአግባብ መያዝ ያለባቸውንም ቅራኔዎችእያጋለጡና እያባባሱ የሚጮሁትም ክፍሎች ይህን ጎጂ ተግባር እንዲያቆሙ መንገር የግድ ይሆናል። ግርግሩ ለወያኔ ሰርጎ ገቦች፤ ለአጥፊ አንጃዎችና ለባዕድ ቅጥረኞቻቸውም እያመቸ ነውና በአስቸኳይ ቢወገድና ሕዝብን ሊመሳሰሉ የተነሱትም ቅጥረኞች ተጋልጠው

ቢገለሉ ለሕዝበ ትግል ጠቃሚ ነው። ህብረት ፈላጊና ጠሪ መስለው ህቀኛ የትብብር ጥረቶችን ሊያኮላሹ የተላኩትንም ቅጥረኞች ሁሉ ማጋለጥ ተገቢ ነው። ህብረት ሊጠነክር የሚችለው የሕዝብ ወገኖች ለወያኔና ቅጥረኞች ዝግ ሆነው ፤ ምስጢራቸውን ጠብቀው፤ ችግሮቻቸውን በውስጣቸው በአግባቡ ፈትተውና የህብረት ጥረታቸውን አጠናክረው ሲገኙ ብቻ ነው።

ለዚህም ነው ኢሕአፓ ህላፊነትን በሚያንፀባርቅ መንፈስ ድርጅቶች ነቅተው በመሥራትና በመታገል ለወያኔ ከፋፋይ ሴራ ሰለባ ሆነው እንዳይገኙ አደራ የሚለው። የሕዝብ ወገን መስለው ግን ድርጅቶችን ገበና ለወያኔ እያሰጡ የሚያሳጡትንና የሚጎዱትንም መሰሪዎች፤ሰርጎ ገቦችና አንጃዎች ሁሉ በጋራ መታገል የሁሉም ግዴታ ይሆናል።



EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France